# CBHC



### የማህበረሰብ የባህሪ ጤና ማዕከል (CBHC) ማለት ምንድን ነው?

የማህበረሰብ የባህሪ ጤና ማዕከላት ሰዎች ለአዕምሮ ጤና እና ለዕፅ ሱሰኛነት ፍላጎቶቻቸው እርዳታ የሚያገኙበትን መንገድ ቀላል ለማድረግ በማሳቹሴትስ ውስጥ የአዲሱ ተነሳሽነት አካል ናቸው። ችግሩ ታዲያ ሰፊውን ማህበረሰብ በማሳተፍ ትግበራ ላይ ቁልፍ ምዕራፍ ነው። የባህሪ ጤና ማሻሻያ ፍኖተ ካርታ እና የባህሪ ጤና ህክምና ተደራሽነትን ለማሻሻል ቁርጠኛ መሆን።

የዕምሮ ጤና እና የአደንዛዥ ዕጽ ተጠቃሚነት አገልግሎት የሚያስፈልጋቸው ሰዎች በ CBHC ጣቢያ ውስጥ ጊዜውን የጠበቀ፣ ከፍተኛ ጥራት ያለው እና በማስረጃ ላይ የተመሰረተ እንክብካቤ ማግኘት ይችላሉ። ይህም መደበኛ ቀጠሮዎችን፣ አስቸኳይ ጉብኝቶችን እና 24/7 የማህበረሰብ-አቀፍ የቀውስ/የአስቸኳይ ጊዜ አገልግሎቶችን ይጨምራል።

## የ CBHC አገልግሎቶችን ማን መጠቀም ይችላል?

በማሳቹሴትስ ውስጥ የሚኖር ማንኛውም ሰው የ CBHC አገልግሎቶችን መጠቀም ይችላል። ማንም ሰው ተከልክሎ እንዲመለስ አይደረግም። ፕሮግራሞቹ በሁሉም እድሜ ላሉ ሰዎች፣ ማለትም - ህጻናትን፣ ጎረምሶችን እና ጎልማሶችን ያገለግላሉ።

### አንድ ሰው የአስቸውኳይ ሁኔታ/ቀውስ ውስጥ ከገባ ምን ማድረግ እችላለሁ?

**በ 833-222-2030 ለCHA የቀውስ መስመር እና ተደራሽነት መደወል ይችላሉ።** የሰለጠነ ሰራተኛ ይረዳዎታል እና የባህሪ ጤና እንክብካቤ ማግኘት እንደሚችሉ ያረጋግጥልዎታል።

**የCBHC አካል እንደመሆኑ መጠን፣ ካምብሪጅ የጤና ህብረት (CHA) በማህበረሰቦቻችን ውስጥ የ24/7 የተንቀሳቀሽ (ሞባይል) የቀውስ አገልግሎቶችን** እየሰጠ ይገኛል። የስነባህሪ ጤና የክሊኒክ ባለሙያዎቻችን ሰዎችን በስልክ ያነጋገራሉ፣ ወይም ሰዎችን በዬቤታቸው ውስጥ፣ በትምህርት ቤቶች ወይም - በካምብሪጅ ሆስፒታላችን ውስጥ የሚገኘውን የባህሪ ጤና አስቸኳይ እንክብካቤ ማዕከልን እና የማልዴን ክብካቤ ማዕከልን ጨምሮ፣ በሌሎች የማህበረሰብ የጋርዮሽ አካባቢዎች በአካል ያገኟቸዋል። ይህ በቀውስ ውስጥ ያሉ ሰዎችን ለማጥናት፣ ፍላጎታቸውን ለመገምገም እና ከእንክብካቤ ጋር ለማገናኘት ያስችለናል። የተንቀሳቃሽ (ሞባይል) የቀውስ አገልግሎቶች ለችግሩ የመድረስ ጊዜ በዋናነት 1 ሰዓት ነው።

ድንገተኛ የህክምና እርዳታ (አደጋ) ባጋጠመዎ ወቅት፣ እባክዎ  ለ911 ይደውሉ።

## ሌሎች ምን-ምን የCBHC አገልግሎቶች አሉ?

የ **24/7 የስልክ መስመር** (833-222-2030) የባህሪ ጤና ቀውስ ውስጥ ያሉትን ሰዎች ፍላጎት ይመለከታል፣ እንዲሁም በአካባቢው ስላለው የባህሪ ጤና አገልግሎት መረጃ ይሰጣል።

CHA በተጨማሪም በካምብሪጅ ሆስፒታል፣ Cambridge Street, Cambridge ውስጥ እና በCHA የማልዴን የእንክብካቤ ማዕከል ውስጥ እንደደረሱ ዘው ብሎ በመግባት የባህሪ ጤና ተደራሽነት/አስቸኳይ የእንክብካቤ አገልግሎት የሚገኝበት ቦታ አለው።

ሌሎች አገለሎቶች፣ ተጨማሪ የአቻ ድጋፍ ቡድኖችን፣ የላቀ የእንክብካቤ አስተዳደርን፣ እና የስሜታዊ ህክምና የማገገሚያ ክትትልን ይጨምራሉ።

*በጀርባው ይቀጥላል*

Cambridge Health Alliance

CARE TO THE PEOPLE

# CBHC



## ወትሮውንም የባህሪ ጤና አቅራቢ ያለኝ ከሆነስ?

ያም ቢሆን፣ መረጃን፣ ድጋፍን እና እንክብካቤን ለማግኘት አሁንም የ CBHC አገልግሎቶችን መጠቀም ይችላሉ። ይህም ታዲያ፣ ለተደራሽነት እና ለቀውስ መስመር በ **833-222-2030** መደወልን፣ ወይም በካምብሪጅ ሆስፒታል **የባህሪ ጤና ተደራሽነት/አስቸኳይ እንክብካቤ አገልግሎት** መጠቀምን ይጨምራል። ቀጣይነት ያለው እንክብካቤዎ አካል እንደመሆኑ ሁሉ፣ ወደ መደበኛ የባህሪ ጤና አቅራቢዎ ሊመሩ/ሊስተላለፉ ይችላሉ።

## ወጪ አለው እንዴ?

የባህሪ ጤና ቀውስ አገልግሎቶች ሁሉም በጤና መድህን (ኢንሹራንስ) ይሸፈናሉ፣ እና የመድን ሽፋን ለሌላቸው ግለሰቦችም አገልግሎቶችን ተደራሽ ያደርጋሉ። ኢንሹራንስ ለሌላቸው ግለሰቦች፣ አገልግሎቶች በብዙሀን-ጤና (MassHealth) ይሸፈናሉ።

በ CBHC የሚሰጡ አብዛኛዎቹ ተመላላሽ የባህሪ ጤና ታካሚዎች አገልግሎቶች በጤና መድን (ኢንሹራንስ) ይሸፈናሉ። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ ለተደራሽነት እና የቀውስ መስመር በ**833-222-2030** በመደወል መጠየቅ ይችላሉ።

## CBHC አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው?

ላለፉት በርካታ ዓመታት ለአእምሮ ጤና እና ለአደንዛዥ ዕጽ ተጠቃሚዎች ፍላጎቶች እንክብካቤ ለማግኘት በጣም አስቸጋሪ ሆኖ ቆይቷል። ብዙ ሰዎች ያለ እንክብካቤ ቆይተው ጤንነታቸው ተጎድቷል። ሌሎች ደግሞ፣ አንዴውኑ እችግር ውስጥ ከወደቁ በኋላ ለአእምሮ ጤና እንክብካቤ የድንገተኛ ህክምና ክፍልን ተጠቅመዋል። ይህም ሆስፒታሎች ውስጥ መጨናነቅ እንዲፈጠር እና ለአእምሮ ጤና ፍላጎቶች ከተገቢው በታች የሆነ እንክብካቤ እንዲኖር አድርጓል።

የማህበረሰብ የባህሪ ጤና ማዕከል ሞዴል በተለይ በችግር ላይ ላሉ ሰዎች አገልግሎቱን የበለጠ ተደራሽ በማድረግ የአእምሮ ጤና እንክብካቤን ለማሻሻል ያለመ ነው።

## እኔ በምኖርበት አቅራቢያ የሚገኙ ሌሎች CBHCዎች አሉ ወይ?

አዎ። በመላው ማሳቹሴትስ ዙሪያ 25 CBHCዎች አሉ።

ካምብሪጅ የጤና ህብረት (ሄልዝ አላያንስ) ለሜትሮ ቦስተን ክልል ከተመረጡት የCBHC ቦታዎች ውስጥ አንዱ ነው። የCHA የአገልግሎት የሚሸፍናቸው ክልሎች፣ ካምብሪጅ፣ ሳመርቪል፣ ኤቨሬት፣ ማልዴን እና ሜድፎርድ ናቸው።
ሌሎች የአካባቢያቸውን ማህበረሰቦች እያገለገሉ ያሉ ሌሎች CBHCዎች የሚገኙባቸው ቦታዎችም አሉ:

**ሰሜን ሳፎክ (North Suffolk) CBHC 888-309-1989**
14 Porter Street, East Boston (14 ፖርተር ስትሪት፣ ምስራቅ ቦስተን)
ይይም ቼልሲን፣ ሬቬሪን፣ ምስራቅ ቦስተንን፣ ዊንትሮፕን፣ እና ቻርለስታውንን በማገልገል ላይ ያለ ነው።

**ቦስተን የሕክምና ማዕከል CBHC**
850 Harrison Ave, Boston (850 ሃሪሰን አቬኑ፣ ቦስተን)
ቦስተንን ፣ ብራይተንን ፣ ብሩክሊንን በማገልገል ይገኛል።

Cambridge Health Alliance

GR24_136